


*በኢትዮጵያ ትግል ውስጥም ሆኜ ልጆቼን ለማሳደግ ያለኝን ሀላፊነት ተወጥቻለሁ:: አሁንም ወደፊትም እወጣለሁ:: ሁለቱም ለእኔ እኩል ግዴታዎች ናቸው:: በነፃነት መኖር እፈልጋለሁ ስል ወደዚህ አለም በእኔ ፍላጎት ያመጣኋቸውን ልጆች ማሳደግና የአባትነት ግዴታ የመወጣት ሀላፊነትንም ይጨምራል:: ወደኋላ የምልበት ጉዳይም አይኖርም:: አንዱን ለማድረግ አንደኛው መቆም አለበት የሚል እምነት ያላቸው ሰዎች ካሉ በአመለካከት ደረጃ በጣም ተሳስተዋል:: ምናልባት ፖለቲካችንንም በጣም የሚያዳክመው የጥቂት አርበኞች እና ጀግኖች ስራ አድርገን ስለምናየው ይመስለኛል:: ሁሌም የምለው ሁሉም ለፖለቲካው የድርሻውን ማድረግ አለበት ነው:: እኔም እንደ ብርሃኑ «በዜግነት ያለኝን ሃላፊነት እወጣለሁ» በሚል ነው እዚህ ውስጥ የገባሁት እንጂ የተለየሁ ጀግና ሆኜ አይደለም :: ወደ ፊትም የተለየ ጀግና መሆን አልፈልግም::* *(ሙሉ ቃለ ምልልሱን በገፅ 8)*

# ንቅናቄው ሲፈተሽ!

